# አቶ ሙሉጌታ መንገሻ አለሙ



(ሰኔ.13 ቀን 1952 ዓ.ም. - ሚያዚያ 29 ቀን, 2015 ዓ.ም. እ.አ.አ.)

## የአቶ ሙሉጌታ መንገሻ አለሙ አጭር የህይወት ታሪክ

አቶ ሙሉጌታ መንገሻ ከአባታቸው ከአቶ መንገሻ አለሙ
እና ከእናታቸው ወ/ሮ ዛብሽ ወርቅ ሥዩም በጎጃም ክፍለ
ሐገር በባህር ዳር አውራጃ በሜጫ
ወረዳ እ.አ.አ ሰኔ 13 ቀን 1952 ዓ.ም. ተወለዱ።
ዕድሜአቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ በመራዊ አንደኛ
ደረጃ ትምህርት ቤት ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን
ደግሞ ጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል።
ከዚያም በ1966 ዓ.ም. በህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ተቀላቅለው
በተለያዩ ሪጅን በታጋይነት እና በኮሚሣርነት አገልግለዋል።
ከዚያም በወቅቱ ወደ ሱዳን ለድርጅት ሥራ ተልከው አገልግለዋል።
በኋላም በተፈጠረው ወቅታዊ ሁኔታ ወደ አሜሪካን አገር በፖለቲካ
ጥገኝነት በ1982 እ.አ.አ. ካሊፎርኒያ ሳንሆዜ የሚባል ከተማ
በመኖር ቫሌ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለ3 ዓመታት ካገለገሉ በኃላ
ወደ ዋሽንግተን እስቴት በመምጣት በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን
በመግባት በፖለቲካል ሳይንስ የባችለርስ ዲግሪያቸውን
በ1991 አግኝተዋል።
በሥራ ዓለም በሲያትል ሀውሲንግ አውቶሪቲ በፕሮጀክት ማናጀርነት
እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል።
አቶ ሙሉጌታ መንገሻ ከመጀመሪያ ባለቤታቸው ከወ/ሮ የሺአረግ
ከበደ፥ ወጣት ሥዩም ሙሉጌታን፣ ከአሁኑ ባለቤታቸው ወ/ሮ ሀረግ
ወይን፥ ሙሉ ቤዛ ሙሉጌታ፣ ቤተልሄም ሙሉጌታና ልዑል ሙሉጌታን
አፍርተዋል።



አቶ ሙሉጌታ መንገሻ ሀገራቸውን ወዳድ ከመሆናቸው የተነሳ ከፍተኛ ሃገር ፍቅር ስሜት የነበራቸውና ጉልበታቸውንም ሆነ ገንዘባቸውን አስተዋጽኦ መባድረግ ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋ። የወንድማችንን ነፍስ በገነት ያኑርልን!  አሜን።

በዚህ ከባድ ሀዘን ጊዜ ከጎናችን በመገኘት ላጻናናችሁን በጉልበት በሃሳብ ወይንም በገንዘብ ድጋፍ ላደረጋችሁልና ሁሉ ከልብ የመነጨ ትልቅ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ባለቤታቸው እና ቤተሰቦቻቸው።